# ከግዛት ውጭ የተሰጡ ፍርዶች አፈፃፀም ሕግ በኢትዮጵያ

በኢብራሂም ኢድሪስ*

## መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን የተለያዩ ሀገሮች የሚያደርጓቸው ልዩ ልዩ ግንኙነቶች ውስብስብና እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ የዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን ያስከትላሉ። ባለፉት ብዙ አስርተ ዓመታት ዓለማችን ያለፈችበት የትራንስፖርትና የመገናኛ ዕድገት ለእንደነዚህ ዓይነት እርስ በእርሳቸው ለሚጋጩ ሁኔታዎች መፈጠር የራሱን ሚና ተጫውቷል። በእነዚህ ሀገሮች፣ በንግድ፣ በመዋዕለ ንዋይ፣ ፍሰት እንዲሁም በሌሎች ምክንያቶች ሳቢያ በተለያዩ ሀገሮች ኗሪዎችና ዜጎች መካከል የተፈጠሩ ግንኙነቶች የተለያዩ የሕግ ሁኔታዎች ከመፍጠራቸውም በላይ እነኝህን የሕግ ሁኔታዎች የአንዱ ሀገር ሕግ የሌላኛውን ተጭኖ ሊቆጣጠራቸውና ሊገዛቸው ሲሻ ይስተዋላል። በተለያዩ ሀገሮች ሕግ መካከል የሚነሳውን ይህን ዓይነት ግጭት ለመታደግ ሀገሮች የየራሳቸውን የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግን አዘጋጅተው በሥራ ላይ ያውላሉ። የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ ሀገሮች የባዕድ ሁኔታዎች የሚገኙበትን ማለትም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሀገሮችን የሚመለከት ጉዳይ ባጋጠመ ጊዜ አግባብነት ያለውን ፍርድ ቤት ለመወሰን፣ ሕግን ለመምረጥ ወይም በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ በሀገር ውስጥ ዕውቅና ሊሰጠው ወይም ተፈጻሚ ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታዎች ለማወቅ ይረዳል።

በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ ገለጻ የሚሰጥበት በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶች ተፈጻሚነት ጉዳይ የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ ዋና አካል ነው። ብዙ ሀገሮች በሌሎች ሀገሮች ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ፍርዶችን ፍርድ ቤቶቻቸው ለማስፈጸም እንዲችሉ በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶችን ለማስፈጸም የሚረዱ ድንጋጌዎችን ያካተተ ሕጎችን አውጥተዋል። ሌሎችም በውጭ ሀገሮች የተሰጡ ፍርዶችን አፈጻጸም በሚመለከት የዓለም አቀፍ ስምምነቶች አካል ሆነዋል።

እንደሌሎች ብዙ ሀገሮች ኢትዮጵያ ከሕግ ግጭት ሁኔታዎች ጋር ተያይዘው የሚመጡትን የውጭ ፍርዶች አፈፃፀም ጉዳዮችን ለመምራት እንዲያስችላት የራሷን ሕግ ደንግጋለች፣ አዘጋጅታለች። የተወሰኑ አንቀጾችን የሚያካትተው ይህ ሕግ በ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ወይም ብያኔ ስለሚፈጸምበት ሁኔታ በሚል ምዕራፍ ሥር ተቀምጦ ይገኛል።

የፍትሐብሔሩ ክፍል እንዲሆን ታስቦ በሬኔዴቪዲ ተዘጋጅቶ የነበረው የዓለም አቀፍ የግል ሕግ በውስጡ የውጭ ሀገር ፍርዶች አፈፃፀምን በተመለከተ ምንም ዓይነት መሠረተ ሀሳቦችን አላካተተም ነበር።

በውጭ ሀገር ስለተሰጡ ፍርዶችና የግልግል ወይም የሽምግልና ውሳኔዎችን የሚመለከቱት የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች በቅርብ ሲመረመሩ እንደሚያረጋግጡት፣ ኋላም እንደምንመለከተው፣ በእነዚህ አንቀጾች ውስጥ የተካተቱትን መርሆዎች ለመረዳትም ሆነ በቀላሉ ለማስፈፀም አስቸጋሪ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የአንድ ሀገር ዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ ማካተት የሚገባቸውን መሠረተ ሀሳቦች ባለማካተታቸው በራሳቸው በቂ አይደሉም። በሀገሪቱም ውስጥ ብቁ የሆነ የፍርድ ቤቶች ል ምድና ጥናታዊ ጽሑፍ ያለመኖሩም የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓቱን ድንጋጌዎች የማስፈጸሙን ችግር ይበልጥ  አባብሶታል። በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ካገኙ ጥቂት ውሳኔዎች መካከል ሁለቱ ብቻ በውጭ ከተሰጡ ውሳኔዎች አፈፃፀም ጋራ የተገናኙ ናቸው። በተጨማሪም ለረጅም ጊዜያት የዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግ ጉዳይ በኢትዮጵያ የምሁራንን ትኩረት ያላገኘ መሆኑ የሕጉን ዕድገት ክፉኛ ገቶታል። ለምሳሌ ፕሮፌሰር ሴድለርም ሆኑ ፕሮፌሰር ሲንገር ለዓለም አቀፉ የግለሰቦች ሕግ ማስተማሪያነት እንዲያገለግሉ ባዘጋጁዋቸው የጥናት ፅሑፎች ላይ የውጭ ውሳኔዎች አፈፃፀምና እውቅናን በተመለከተ ምንም ነጥቦችን አላነሱም።

---

* የሕግ ረዳት ፕሮፌሰርና የቀድሞ የሕግ ፋኩልቲ ዲን፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ከ1928 እስከ 1933 በቆየው የኢጣሊያን ወረራ ማግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ከውጭ ሀገር ዜጎች ጋር በይበልጥ የሚገናኙበት ሁኔታ ከመፈጠሩም በላይ በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ብዙ ኢትዮጵያውያን በጎረቤትና ራቅ ባሉ ሀገሮች መኖር ሲጀምሩ ብዙ የውጭ ሀገር ዜጎችም ለአጭር ጊዜም ሆነ ለዘለቄታው በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ጀምረዋል። በአሥራ ሰባቱ ዓመታት የደርግ አገዛዝ ወቅት ኢትዮጵያውያን በከፍተኛ ቁጥር ወደ ውጭ ፈልሰዋል። ባለፉት ጥቂት ዓመታትም ሀገሪቱ በምትከተለው የነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሳቢያ ከውጭው ዓለም ጋር ያላት ግንኙነት መሻሻልን አሳይቷል። ኢትዮጵያ ለውጭ የመዋዕለ ንዋይ አፍሳሾች በሯን ክፍት በማድረጓም ዓለም አቀፋዊ የንግድ ግንኙነቶቿ በከፍተኛ ሁኔታ በማደግ ላይ ናቸው።

ያለጥርጥርም እነኝህና ሌሎች ከውጭ ዓለም ጋር የሚደረጉ የፖለቲካ፣ የሶሻልና የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ከፍተኛ የውጭ ግንኙነት ዕድገት እንዲከሰት በማድረጋቸው ይህም በራሱ በኢትዮጵያና በተለያዩ ሀገሮች ሕጎች መካከል ግጭት እንዲፈጠር ሁኔታዎችን አመቻችቷል። በመሆኑም ኢትዮጵያ፣ ሕጎቿን በተለይም በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ የሚገኙና በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶችን አፈፃፀም የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የውጭ ፍርዶችን በተመለከተ የማይቀሩና ውስብስብ እየሆኑ የሚመጡ ችግሮችን ለመፍታት በሚያስችል መልኩ በቂ ሆነው ይገኙ ዘንድ መከለስና ማዘጋጀት ይኖርባታል።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከኢትዮጵያ ክልል ውጭ የተሰጡትን ውሣኔዎች አፈፃፀም ላይ የሚቆጣጠሩትን የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎችን ለመተንተን ከመሞከሩም በላይ ሕጉ ባልዳሰሳቸው ችግሮች ላይ መፍትሔ ለከጠቆም ሙከራ ተደርጓል። እንዲሁም በማድረግ ጽሑፉ የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥርዓት ሕግን ለመከለስ አስፈላጊነትን ከመጠቆሙም በላይ ሕጉን በማስፈፀም ሒደት ውስጥ ፍርድ ቤቶች እየተጋፈጡት ያለውን ችግር የመቅረፊያ ዘዴዎችን ይዘረዝራል።

የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ ሁኔታዎች ያሉባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ከሚሰጧቸው ውሳኔዎች ልምድ እንደሚታየው፣ ፍርድ ቤቶቹ የአጋጠማቸውን የሕግ ችግሮች ለማቃለል ሊረዱ የሚችሉ ተስማሚ የሆኑ ድንጋጌዎች ለማግኘት ባልቻሉ ጊዜ ፊታቸውን ወደ ውጭ ሀገር ሕጎችና ተቀባይነት ወደአላቸው ልምዶች የማዞር ልምድ አላቸው። በዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ ውስጥ የግል ሁኔታን በተመለከተ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት እንደ መሠረት ሆኖ ሊያገለገል የሚገባው የዜግነት ወይንስ የመኖሪያ ቦታ መርህ መሆን አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ ግልጽ ሆኖ የተቀመጠ ሕግ በማጣቱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወደ ውጭ ሀገር ሕግ ፊቱን ያዞረበት ወቅት ነበር።[1] በተመሳሳይም የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ ጉዳይን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ብይን ለመስጠት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መሠረተ ሀሳብ ከዚህ ጽሑፍ ሊያገኙ እንደሚችሉ የጸሐፊው እምነት ነው።

## ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ የተሰጠ ፍርድ አፈፃፀም መሠረት ሀሳቦች

አንድ ሀገር ምንም ዓይነት ዓለም አቀፋዊነትን የምታራምድ ብትሆንም እንኳን ከክልሏ ውጭ የሚሰጡትን ፍርዶችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ታስፈፅማለች ማለት አይደለም[2]። ጉዳዩን ሊቆጣጠሩ የሚችሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ድንጋጌዎች በተቃራኒው እስካልደነገጉ ድረስ የውጭ ፍርድን ተፈፃሚ እንድታደርግ የተጠየቀችው ሀገር ለፍርዱ መፈፀም በሕጓ ውስጥ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ትጠይቃለች።

---

1 ሀሎክ በ· ሀሎክ (የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቁጥር 24750) የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወደ ውጭ ፍርድ ሕግና ልማድ የማተኮር አስፈላጊነት ምክንያትን አቅርቧል። ፍርድ ቤቱ እንዳስቀመጠው "የውጭ ዜጎችን ሁኔታ በሚመለከቱና የሕግ ግጭት በሚያመጡ ጉዳዮች ላይ ፍርድ ቤቶች የሚኖራቸውን ሥልጣን በሚመለከት ወይም የዓለም አቀፍ የግለሰቦችን ጉዳይ የሚቆጣጠር ሕግ ድንጋጌ በኢትዮጵያ ውስጥ የለም። ስለዚህም ጉዳዩን ሊገዛ የሚችል የሀገር ውስጥ ሕግ በጠፋ ጊዜ በሌሎች ሀገሮች ተቀባይነት ያላቸውን የዓለም አቀፍ የግለሰቦች መሠረታዊ ሀሳቦችን መከተል የግድ ይሆናል"።

2 ሮበርት ኤን ሆርኒክ፣ ከግዛት ውጭ የተሰጠ ውሳኔ እውቅናና ተፈፃሚነት በኢንዶኔዢያ፣ ሀርቫርድ የሕግ መጽሔት፣ ቮልዩም 18፣ 1997፣ ገጽ 77-88

በዓለም አቀፍ ሕግ በአሁኑ ጊዜ ሁለት ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸው ከክልል ውጭ የሚሰጡ ፍርዶች አፈፃፀም ዘዴዎች አሉ[3]። የመጀመሪያው የአፈፃፀም ዘዴ በኮንቲነንታል አውሮፓና በደቡብ አሜሪካ በስፋት ይሠራበታል። በእነዚህ አካባቢዎች በሚገኙ ሀገሮች ሕግ መሠረት አንድ ከክልል ውጭ የተሰጠ ፍርድ ተፈፃሚነትን ሊያገኝ የሚችለው ውሳኔውን እንድታስፈጽም የተጠየቀችው ሀገር ሕገ ደንቦች የሚያስቀምጧቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ሲያሟሉና ውሣኔው እንደገና ታይቶ በጽሑፍ ኤክስኳቱር (exequatur)[4] ሲረጋገጥና ሕጋዊ እውቅና ሲሰጠው ነው[5]። በእነኚህ ሀገሮች ውስጥ አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት ይህንን በተመለከተ ግልጽ የፍርድ ቤት ውሣኔ ሊሰጥበት ያሻል። ስለዚህም የውጭ ሀገር ፍርድ በራሱ ብቻውን ተፈፃሚ አይሆንም ማለት ይቻላል[6]።

ሁለተኛው የአፈፃፀም ዘዴ ደግሞ በአንግሎ አሜሪካን ሕግ ተገላጭነት ያለው ነው[7]። የግሎባል አሜሪካንን ሀ የሕግ ሥርዓት በሚከተሉት ሀገሮች ሕግ መሠረት አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችለው በሀገር ውስጥ ተጨማሪ ፍርድ ድጋፍ አግኝቶ የመጨረሻ ፍርድ እንደሆነ ሲረጋገጥ ነው። በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ በማያጠራጥር መልኩ እንደሚፈፀም በፍርድ ተቀባይነትን ሊያገኝ የሚችለው እንዲፈፀም በሚፈለግበት ሀገር ሕግ ውስጥ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች ሲያሟላ ብቻ ነው[8]። ለምሳሌ በእንግሊዝ ሀገር ሕግ መሠረት አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ በራሱ ለተፈፃሚነት ብቁ ሆኖ የሚገኝባቸው ሁኔታዎች በዝርዝር ተቀምጠዋል። እነሱም፡-

ሀ) "እንዲፈፀም የተጠየቀውን ፍርድ የወሰነው ፍርድ ቤት የሚገኝበት ሀገር በእንግሊዝ ሀገር የተሰጠውን ፍርድ የሚፈጽም መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ለ) ፍርዱ የተሰጠው በሕግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት መሆኑ ሲታወቅ፤

ሐ) የፍርድ ባለዕዳው ቀርቦ መከላከያውን ለማሰማት ዕድል የተሰጠው መሆኑ ሲረጋገጥ፤

መ) ፍርዱ የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያለው መሆኑ ሲታወቅ፤

ሠ) የፍርዱ መፈጸም ከሕዝብ ሞራልና ፀጥታ ጋር ተቃራኒ ያለመሆኑ ሲታወቅ፤"[9]

በዩናይትድ ስቴትስ በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶች አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች እስከተሟሉ ድረስ እውቅናና ተፈፃሚነትን ሊያገኙ ይችላሉ። ለምሳሌ በሂልተን እና ጉዮ መካከል በተነሳው ክርክር ውስጥ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ተዘርዝረዋል። አንደኛ/ በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት የተሰጠው ፍርድ ግልጽና ነፃ በሆነ የፍርድ ሂደት የተሰጠ መሆን አለበት፤ ሁለተኛ/ ፍርዱን የሰጠው የውጭ ሀገር ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ያለው ሊሆን ይገባል፤ ሦስተኛ/ የውጭ ሀገሩ ፍርድ ቤት የፍርዱን ሂደት መደበኛ በሆነ ሂደት ያካሄደ መሆን ይኖርበታል፤ አራተኛ/ ተከሣሹ አግባብነት ባለው መንገድ መጥሪያ እንዲደርሰው የተደረገ ወይም በፈቃዱ በፍርድ ቤቱ ፊት የቀረበ ሲሆን፤ አምስተኛ/ ፍርዱን የሰጠው አካል በራሱ ዜጎችና ዜጎቹ ባልሆኑ ሰዎች መካከል ልዩነት ሳይፈጥር ሊሰራ የሚችል የፍትሕ ሥርዓት ሲኖረው፤ ስድስተኛ/ ፍርዱን በሰጠው የውጭ ሀገር ፍርድ ቤት፤ ፍርዱ በተመሠረተበት የሕግ ሥርዓት ወይም የተገኘበት አላግባብ የሆነ ዘዴ ላይ ጥላቻ የሚያስነሳ

---

3 ኧርነስት ጂ· ሎሬንዘን፤ በውጭ የአሜሪካን ውሣኔዎች አፈፃፀም ዮል የሕግ መጽሔት፡ ቮል ዩም 29፡ 1919–20፡ ገጽ 192–193

4 ኤክሰኳቱር/exequatur በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድን እንደ አዲስ ማየት ማለት ነው።

5 ኧርነስት ጂ· ሎሬንዘን፤ ገጽ 193

6 ከሕግ አንፃር ከግዛት ውጭ የተሰጠን ውሣኔ የመደምደሚያ ተፈፃሚነት መንፈግ በፈረንሳይ የተጀመረው ኮድ ሚቹድ (Code Michoud) ሕግ በ1629 ከፀደቀ ወዲህ ነው። ለበለጠ ማብራሪያ የኩርት ኤ ሔልድልማን የአሜሪካን የገንዘብ ውሣኔ በውጭ ተቀባይነት ያለማግኘቱ "መፍትሄውስ"፡ አዩዋ የሕግ መጽሔት፡ ቮልዩም 42፤ 1957፡ ገጽ 238 ይመልከቱ

7 ኧርነስት ሎሬንዘን፤ ገጽ 193

8 በኮመን ሎው ሕገ ሥርዓት ከግዛት ውጭ የተሰጠን ውሣኔ መደምደሚያ ተፈፃሚነት መስጠት እንዳለበት በግልጽ የተቀመጠው በካናዳ በተሰጡ ውሣኔዎች ላይ የዌስት ሚኒስቴር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሣኔ ነው። የካናዳ የጠበቆች ምክር ቤት መጽሔት ቮልያም 39፤119604 ገጽ የጎደርድ ኮግሬይ (1870) L.L.6. Q.B. 139 ይመልከቱ።

9 የውጭ ሀገር ፍርዶች (እንካ በእንካ መርህ ላይ የተመሠረቱ የፍርድ አፈጻጸሞች) ደንብ፡ ሲ. 13፡ አንቀጽ ከ1 እስከ 5 አር ኤች ግራቭሰን፡ ዘ ኮንፍሊክት ኦፍ ሎው 6ኛ እትም 1969 ገጽ 663–680

ሁኔታ ከሌለ ወይም ፍርዱን በዩናይትድ ስቴትስ ለምን መፈጸም እንደማይገባው የሚያስረዱ ሌሎች የተለዩ ምክንያቶች ሳይቀርቡ ሲቀርና፣ ሰባተኛ/ ፍርዱን የሰጠው ሀገር ሕግ ለዩናይትድ ስቴትስ ፍርድ እውቅና የሚሰጥና የሚያስፈጽም ሲሆን የሚሉት ናቸው[10]።

የኢትዮጵያን ሕግ ቀረብ ብለን ስንመለት ከዚህ በላይ ከጠቀስናቸው ሁለት የውጭ ፍርዶች አፈፃፀም ዘዴዎች መካከል ሁለተኛውን የተቀበለ አካሄድ ነው። ወደ ኋላ ለማየት እንደሚሞከረው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ተፈፃሚነት ለማግኘት በሀገር ውስጥ ፍርድ መጠናከርና መረጋገጥ ይጠበቅበታል። እንዲህ ዓይነት ፍርድ ለመስጠት ደግሞ ፍርድ ቤቶች በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ውሣኔ የተጠቀሱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።[11] የኢትዮጵያን ሕግ ከዩናይትድ ስቴትስና ከእንግሊዝ ሕጎች በምናነፃፅርበት ወቅት የእነዚህ የሁለት ሀገሮች ሕጎች ያስቀመጡዋቸው አብዛኞቹ ቅድመ ሁኔታዎችና የኢትዮጵያ ሕግ የሚዘረዝራቸው ቅድመ ሁኔታዎች ተመሳሳይነት እንዳላቸው ይታያል። የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 458 ያስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፣

ሀ) እንዲፈጸም የተጠየቀውን ፍርድ የወሰነው ፍርድ ቤት የሚገኝበት አገር በኢትዮጵያ የተሰጠውን ፍርድ የሚፈጽም መሆኑ ሲረጋገጥ፣
ለ) ፍርዱ የተሰጠው በሕግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት መሆኑ ሲታወቅ፣
ሐ) የፍርድ ባለዕዳው ቀርቦ መቃወሚያውን ለማሰማት መብት የተሰጠው መሆኑ ሲረጋገጥ፣
መ) ፍርዱ የመጨረሻና ተፈጻሚነት ያለው መሆኑ ሲታወቅ፣
ሠ) የፍርዱ መፈጸም ለሕዝብ ሞራልና ጸጥታ ተቃራኒ ያለመሆኑ ሲታወቅ”

የኢትዮጵያ ሕግ እነዚህን ለአንድ የውጭ ፍርድ ተፈፃሚነት እንደ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲያገለግሉ ይፈቅዳል። በይበልጥም ዓለም አቀፍ ስምምነት በሌለበት ወቅት የመሠረተ ሀሳቦቹ ጠቀሜታ የጎላ ይሆናል። ፀሐፊው እስከሚያውቀው ድረስ ኢትዮጵያ በውጭ ሀገር የሚሰጡ ፍርዶችን ተፈፃሚነትን በተመለከተ የአንድም ዓለም አቀፍ ስምምነት አባል አይደለችም። ስለዚህም እንደዚህ ዓይነት ስምምነቶች በሌሉበት ባሁኑ ወቅት በፍትሐ ብሔር የሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸው የግድ ነው[12]።

---

10 ሂልተን ቡጉዮ፣ 159 አሜሪካ፣ 113

11 ኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነርዓት ሕግ፣ አንቀጽ 456(1)

12 የኢትዮጵያ ሕግ ከግዛት ውጭ የተሰጡ ውሣኔዎች እውቅና ሊያገኙ የሚችሉባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በተመለከተ የሚናገረው ነገር የለም። በውጭ ሀገር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሣኔዎችን እውቅና የሚመለከቱ ነጥቦች በኢትዮጵያ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ ያለመመልከታቸው ጉዳይ ሆን ተብሎ የተደረገ ነው የሚል እምነት ፀሐፊው የለውም። ይልቁንም ለደንቦቹ በኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ ያለመካተታቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ። በመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐ ብሔር የሥነ ስርዓት ሕግ እንደ ፍትሐ ብሔር ሕጉ የሕግ ኰሚሽን ተደርጎለት በፓርላማው የፀደቀ ሕግ አይደለም። ይልቁንም ሕጉ ፓርላማው በእረፍት ላይ በነበረበት ጊዜ በቀድሞው ንጉሥ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በድንጋጌ (decree) መልክ የወጣ ነው። ይህም ሆኖ እንኳን እንደሌሎቹ ድንጋጌዎች የ1955 ሕገ መንግሥት አንቀጽ 92 በሚጠይቀው መሠረት ለፓርላማው የቀረበ ባለመሆኑ ተሻሽሎ ሊወጣ አልቻለም። በሁለተኛ ደረጃ የሕጉ ረቂቅ የአንድ ሰው የሥራ ውጤት ብቻ ነበር ለማለት ያስደፍራል። ረቂቁ የ1908 የሕንድ የፍትሐ ብሔር ሥነ ስርዓት ሕግ ቅጅ ሲሆን ከአስፈላጊ ገላጭ ዶክመንቶች ጋር የቀረበ አልነበረም። ይበልጡንም እንደሌሎቹ የኢትዮጵያ ሕጎች በአቀራረፅ ሂደቱ ውስጥ ምንም ዓይነት ጥናትና ውይይት ስላልተደረገበት የውጭ ውሣኔዎችን አፈፃፀም ሕግ በተመለከተ ሊካተቱ የሚገባቸው ነጥቦች ሳይካተቱ ቀርተዋል። ይህ እንዳለ ሆኖ ሊታወቅ የሚገባው አንድ ነገር ቢኖር የውጭ ውሣኔ እውቅና የመስጠቱ ጉዳይ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት አንድ ቅድመ ሁኔታ ስለሆነ ውሣኔው ለተፈፃሚነት ብቃቱ እስከተረጋገጠ ድረስ እውቅና ማግኘት ይገባዋል ወይንስ አይገባውም የሚለው ጉዳይ እምብዛም አከራካሪ ሊሆን አይችልም። እውቅና የማግኘቱ ጉዳይ አስፈላጊነቱ አከራካሪ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ጉዳዩ ሊፈታ የሚችልባቸው አንድ አንድ አማራጮች አሉ። እነሱም ሀ) የአንድ ውሣኔ ተፈፃሚነት የማግኘት ሁኔታ ተቀባይነትንም ስለማያጠቃልል በፍትሐ ብሔር የሥነስርዓት ሕግ የተካተቱ ተፈፃሚነትን የሚዳስሱ ድንጋጌዎች ተቀባይነትም ላይ እንዲሰሩ የማድረግ ሥልጣን ፍርድ ቤቶች አላቸው፣ ለ) በሌሎች ሁኔታዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ ከሌሎች አገሮች ልምዶች ለኢትዮጵያ ሁኔታ ተገቢ ናቸው የሚሉትን ፍ/ቤቶቹን ተቀብለው ሥራ ላይ እንዲያውሉ ማድረግ ናቸው።

በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶች በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንዲፈጸሙ መሟላት የሚገባቸው በኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ ውስጥ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከዚህ በታች የሚገባቸው በኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ ውስጥ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከማየታችን ትንተና ተሰጥቶባቸዋል። ይሁን እንጂ ሕጉ ያስቀመጣቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ከማየታችን በፊት ተቀባይነት ያለውን በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶችን አፈፃፀም ሥርዓት አካሄድ መገንዘብ ይኖርብናል።

## በውጭ ሀገር የሚሰጡ ፍርዶች አፈፃፀም ሥርዓት

አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ተፈፃሚነት ከማግኘቱ በፊት ጉዳዩን በተመለከተ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ማስገባት እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሕግ ይደነግጋል[13]። ይህንን ዓይነት ማመልከቻ የመቀበል ሥልጣን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶታል[14]። ማንኛውም ፍርድ እንዲፈጸምልኝ የሚል ጥያቄ በጽሑፍና ፍርዱ የመጨረሻና የሚፈጸም ስለመሆኑ የሚገልጽ ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ሬጂስትራር ፊርማ ከተደገፈ ሰርቲፊኬትና[15] ከዋናው ፍርድ ቅጂ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል[16]።

የፍርዱን ቅጂ በተመለከተ ሁለት ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። አንደኛው ጥያቄ ፍርዱ ከተሰጠባቸው ማናኛቸውም ቋንቋዎች ወደፌዴራሉ ፍርድ ቤት የሥራ ቋንቋ ወደሆነው ወደ አማርኛ ቋንቋ መቀየር አለበት? የሚለው ነው[17]። ለምሳሌ፣ በቺሊ[18]፣ በኮሎምቢያና[19] በተለያዩ የደቡብ አሜሪካ ሀገሮች እንዲሁም በቀድሞዋ የሶቪየት ሕብረት[20] አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ተፈፃሚነት ከማግኘቱ በፊት ፍርዱን አስፈፃሚ ወደሆነው ሀገር ኦፊሴየላዊ ቋንቋ መተርጎም አለበት[21]። የቬንዙዌላ ሕግ ደግሞ ሕጋዊነቱ የተረጋገጠ የውሣኔው ቅጂ መኖሩን እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ አስቀምጦታል።

በቺሊ ሕግ መሠረት አንድ በሌላ ቋንቋ የቀረበ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድን የውሣኔውን ተፈፃሚነት በጠየቀው ከፍል እንዲተረጎም ሲጠየቅ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ትርጉሙን ከተቃወመ ውሣኔው በኦፊሴላዊ ተርጓሚ እንዲዘጋጅ ይደረጋል[22]። በብራዚል ሕግ መሠረት ደግሞ አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ከአንድ የፖርቱጋል ቋንቋ ትርጉም ቅጂ ጋር መያያዝ ሲኖርበት የትርጉም ሥራውም ኦፊሲያላዊ ደረጃ ባለው ተርጓሚ መዘጋጀት አለበት[23]።

በሁለተኛው ደረጃ ሊነሳ የሚችለው ነጥብ በውጭ የተሰጠው ፍርድ በተሰጠበት ሀገር በሚገኝ የኢትዮጵያ ቆንስላ መረጋገጥ አለበት? የሚለው ነው። በብዙ ሀገሮችና በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ይህ ዓይነቱ ሁኔታ እንዲሟላ ይጠየቃል[24]። ለምሳሌ በብራዚል ሕግ አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ እዚያ አገር ባለ በብራዚል ቆንስላ ሊረጋገጥ ይገባዋል[25]።

ወደ ኢትዮጵያ ሕግ በምንመለስበት ጊዜ በውጭ ሀገር የተሰጠን ፍርድ ወደ አማርኛ ቋንቋ መተርጎም ወይም ፍርዱን በኢትዮጵያ ቆንስላ ጽሕፈት ቤት የማረጋገጥ ቅድመ ሁኔታዎች በግልፅ አልተቀመጡም። በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 457 መሠረት አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት እንዲፈጸም

---

13 የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 456(1)
14 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ ዓመት 2፣ ቁጥር 13፣ 1988፣ አንቀጽ 11(2)(ሀ)
15 የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 457(ለ)
16 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 457 (ሀ)
17 የኢትዮጵያ የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፤ 1987 አንቀጽ 5(2)
18 አልፍሬድ ኢቸበሪ እ፤ የአሜሪካ ቺሊ የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ፤ 1960፤ ገጽ 88
19 ፋኖር ጂ· ኤዶር· አሜሪካ ኮሎምቢያ የዓለም አቀፍ ሕግ 1956 ቦ· 72
20 የራሽያ የፍትሐ ብሔር ሕገ መሠረታዊ ሀሳቦች አንቀጽ 63
21 ሪቻርድ ኤስ· ሎምባርድ አሜሪካ ቬንዙዌላ የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ፤ 1956፣ ገጽ 103·
22 አፕስሬድ ኢቸበሪ እ ኤክ፤ 1960 ገጽ 88
23 ፓል ግሪፍ ጋርላንድ አሜሪካ ብራዚል የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሐግ 1959ዘ ገጽ 93
24 የ1905 የሄግ ኮንቬንሽን አንቀጽ 19፤ 1960ኛውን የሄግ ኮንቬንሽንንም ይመልከቱ
25 ፓል ግሪፍስ ጋርላንድ፤ 1959 ገጽ 93

በሚቀርብበት ወቅት ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይንም ሬጂስትራር መረጋገጥ ይኖርበታል። በተጨማሪም ከውሳኔው ቅጂ ጋር ተያይዞ የውሳኔውን ተፈፃሚነት የሚጠይቅ ማመልከቻ መቅረብ ይኖርበታል። በሌላ በኩል ጉዳዩን በተመለከተም ብዙ ጊዜ ሲሰራበት የቆየውን የፍርድ ቤቶች ሥርዓት ልማድ ማገናዘቡ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በዚህም መሠረት ማንኛውም በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት እንዲፈፀም በሚጠየቅበት ወቅት ወደ አማርኛ እንዲተረጎም ከመጠየቁም በተጨማሪ ውሳኔው በተሰጠበት ሀገር በሚገኝ ኢትዮጵያዊ ቆንስላ እንዲረጋገጥ ይደረጋል።[26]

በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ተፈፃሚነት እንዲያገኝ ማመልከቻ የቀረበለት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የፍርዱ ባለዕዳ ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ቀን እራሱን እንዲከላከል ዕድል እንዲሰጠው ይጠየቃል[27]። ፍርድ ቤቱ ሌላ መጣት መፈቀድ አለበት ወይንስ የለበትም በሚለው ጉዳይ ላይ ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል[28]። አጠራጣሪ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ጥርጣሬዎች እስኪፈቱ ድረስ ፍርዱን ከተፈፃሚነት ሊያግድ ይችላል[29]። በመርህ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ፍርዱን የሚሰጠው የቀረበለትን ማመልከቻ ተመርኩዞ መሆን ይኖርበታል። ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ፍርድ ቤቱ ለምሳሌ የፍርድ ባለዕዳው በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶች በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ተፈጻሚነት እንዲያገኙ መሟላት ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ከሆኑት መካከል አንዱ ሁኔታ አልተሟላም በማለት የውጭ ሀገር ፍርድ እንዳይፈጸም ተቃውሞ ያቀረበ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በሁለቱ ወገኖች መካከል የሚደረገው ክርክር እንዲቆም ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል[30]። ማመልከቻው ተቀባይነትን አግኝቶ የተሰጠው ፍርድ እንዲፈፀም ከተፈቀደ ፍርዱ ልክ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተሰጠ ተደርጎ ሲፈጸም[31] ፍርድ ቤቱም ኪሣራን በተመለከተ ውሣኔ ማሳለፍ ይችላል[32]።

## የእንካ በእንካ ወይም የጋራ ጥቅም ስምምነት (Reciprocity)

እንካ በእንካ በኢትዮጵያ ሕግ አንድ የውጭ ፍርድ ከመፈፀሙ በፊት መሟላት ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ሆኖ ተቀምጧል። በፍትሐ ብሔሩ ሥነ ሥርዓት ሕግ እንደተደነገገው አንድ የውጭ ፍርድ በኢትዮጵያ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችለው ፍርዱ በተሰጠበት ሀገር ውስጥ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ተፈፃሚነት ሊያገኝ የሚችል ከሆነ ብቻ ነው[33]። ይህ አቋም በብዙ ሀገሮች ሕግ ሥርዓት ተቀባይነት አለው[34]። ከዚህ ጋር አያይዘው ሮበርት ሴድለር እንደገለፁት፣

> "በአንድ ሀገር የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የኢትዮጵያን ፍርዶች ለማስፈፀም ፈቃደኞች ሆነው ካልተገኙ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ሁኔታ በዚያ ሀገር ውስጥ የሚሰጡ ፍርዶች ተፈጻሚ እንዳይሆኑ ያግዳሉ። በተቃራኒው እስካልተረጋገጠ ድረስ የሌሎችን ሀገር ፍርዶች የሚያስፈፅሙ ሀገሮች የኢትዮጵያንም ፍርድ እንደሚያስፈጽሙ ተደርገው መወሰድ ይኖርባቸዋል"[35]።

በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድን ተፈፃሚነት በመቃወም የፍርድ ባለዕዳው ውሣኔውን የሰጠው የውጭ ሀገር ፍርድ ቤት የኢትዮጵያን ፍርድ እንደማያስፈጽም በማረጋገጥ ጉዳዩን እንደ አንድ መቃወሚያ ማቅረብ ይችላል። የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት በፍርድ ባለዕዳው የቀረበውን መቃወሚያ የተቀበለው እንደሆነ ተቃውሞ የቀረበበትን የውጭ ሀገር ፍርድ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ያደርጋል። ፍርዱን የሰጠው ሀገር የሌሎቹን ሀገሮች ፍርዶች

---

26 መሐመድ ዓሊ. ሙጃሂድ ከኢትዮጵያ ልዩ ፍርድ ቤት አቃቢ፣ ሕግ ያገባኝ ፋይል ቁጥር 47 ጸ (22/7 1979 አ·አ·)፤ ከአንዳንድ ዳኞች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣

27 የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 459 (1)

28 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 459(2)

29 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 459(3)

30 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 460(1)

31 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 460(3)

32 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 460(2)

33 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 458(ሀ)

34 ኢስታቫን ሣዚ. የዓለም አቀፍ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት፣1967 ገጽ 186

35 ሮበርት ኤ·ሴድለር፣ የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ 1968 ገጽ 394·

እንደሚያስፈጽም የማረጋገጥ መንገድን በተመለከተ ሀገሮች የተለያዩ ልምዶች አሏቸው። በዩናይትድ ስቴትስ ጉዳዩ የሚረጋገጠው ፍርድ እንዲፈጸም በተጠየቀበት ሀገር በጥብቅና ሥራ ላይ የተሰማሩ ሁለት ሰዎች ምስክርነት ሲሰጡ ነው[36]። የቬንዙዌላ ሕግ እንደሚያስቀምጠው ከሆነ ደግሞ ፍርድ ቤቶቹ እንካ በእንካ ስለመኖሩ እርግጠኛ መሆን አለባቸው[37]።

የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ1895 በሂልተንና በጉዮ መካከል ተነስቶ በነበረው ጉዳይ ላይ ፍርድ ከሰጠበት ወቅት ጀምሮ በመሠረተ ሀሳቡ በአንድ ሀገር ላይ የሚወሰድ የበቀል እርምጃ የሆነው የእንካ በእንካ አሠራር ግለሰቦችን ያጉላላል፤ ይበድላል[38] በሚል ከፍተኛ ውዝግብን አስነስቷል። ከዚህም ጊዜ በኋላ የእንካ በእንካን ሥርዓት እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ በተንተራሱ የፍርድ ቤቱ ፍርዶች ላይ ትችት ሲሰጥባቸው ቆይቷል። ቅድመ ሁኔታ በተንተራሱ የፍርድ ቤቱ ፍርዶች ላይ ትችት ሲሰጥባቸው ቆይቷል። ውሣኔውን በሰጠው ሀገር ፖሊሲ ሳቢያ የውጭ ሀገር ተሟጋች ችግር እንዲፈጠርበት ስለሚያደርግ የእንካ በእንካ አሠራር እንዲቆም ብዙዎች አስተያየታቸውን ሲሰነዝሩ ይታያሉ[39]።

እዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው አስፈላጊ ጉዳይ ብዙ ሀገሮች የእንካ በእንካ አሠራርን እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ በግልጽ አያስቀምጡትም። አርጀንቲና እንካ በእንካን በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድን ለማስፈፀም እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ ከማያዩት የደቡብ አሜሪካ ሀገሮች መካከል አንዷ ናት[40]። በብራዚልም ቢሆን አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ተፈፃሚነትም ሆነ ተቀባይነት የሚኖረው የእንካ በእንካን ቅድመ ሁኔታ በማሟላቱ አይደለም። በዩናይትድ ስቴትስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሂልተንና ጉዮ ላይ ከተሰጠው ፍርድ ለየት ባለ መልኩ እንደ ኒዮርክና ካሊፎርኒያ ያሉ ክልሎች የእንካ በእንካን አሠራር አል ተቀበሉትም[41]። ነገር ግን ኢትዮጵያን ጨምሮ በአንዳንድ ሀገሮች የእንካ በእንካ አሠራር ጉል ህ የሆነ ሚና ተጫውቷል[42]። በመጫወትም ላይ ይገኛል።

## በትክክል የተቋቋመና ሕጋዊ ፍርድ ቤት

የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በውጭ ሀገር የሚሰጡ ፍርዶችን የሚያስፈጽሙ ፍርድ ቤቶችን በተመለከተ ሁለት ነጥቦችን ይዳስሳል። እነሱም ፍርድ ቤቶች በትክክለኛ መንገድ መቋቋማቸውና ሕጋዊ ሆነው የመገኘታቸው ሁኔታ ነው[43]። እነኝህን ቅድመ ሁኔታዎች በምናይበት ጊዜ የውጭ ሀገሩ ፍርድ ቤት የተቋቋመበትና ሕጋዊነትን ያገኘበት አግባብነት ያለው ሕግ የቱ መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል። ይህ ጉዳይ ሊወሰን የሚገባው በኢትዮጵያ ሕግ፤ በውጭ ሀገሩ ሕግ፤ ወይንስ በዓለም አቀፍ ሕግ፤ መሆን አለበት ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ መሻት ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ከጥያቄው አኳያ የበላይነት ሊኖረው የሚገባው የኢትዮጵያ፣ የውጭ፣ ወይንስ የዓለም አቀፍ ሕግ በሚለው ጉዳይ ላይ ቁርጥ ያለ መልስ አይሰጥም። በመሆኑ የቅድመ ሁኔታውን አፈፃፀም አስቸጋሪ ያደርገዋል።

---

36 ሪቻርድ ኤስ ሎምባርድ፡ የአሜሪካና የቬኔዝዌላ የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ፣1965 ገጽ 98

37 ዝኒ ከማሁ

38 አልበርት ኤ ኤርዝዊግ እና ኤሪክ ጃይም ፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው፣ 1973፣ ገጽ 53

39 የአሜሪካ የሕጉች ግጭት ሪስቴትመንት የእንካ በእንካ መሠረተ ሀሳብን አይቀበልም፣ በአንቀጽ 434(ለ) ላይ የተጻፈው ትችት

40 ዎርነር ጎልድሹሚት እና ጆዝ ሮድሪጌዝ ኖቪስ የአሜሪካና የአርጀንቲና 1973፣ ገጽ 53

41 ባርባራ ኩልዘር ስለውጭ ውሣኔዎች አፈፃፀም አንዳንድ ነጥቦች፤ ቡፋሎ የሕግ መጽሔት ቮል ዩም 16፤ 1966 ገጽ 90–91 ምንም እንኳን በሂልተንና በጉዮ ውስጥ የተካተተው መሠረተ ሀሳብ ባይሻርም በኤሪና አር አር ቶምኪንስ ጉዳይ ላይ በግልጽ እንደሚታየው በተለያዩ የዓለም አቀፍ ግለሰቦች ሕግ የአሜሪካ ክልሎች የእንካ በእንካ አሠራር ተቀባይነትን እያጣ በመሄድ ላይ ይገኛል። ክልሎች በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊያስቀሩት ይችላሉ። (የኩራካኦ ደሴት ክልል ከ ሳሊትሮን ዲቫይሲስ ኩባንያ 489 ኤፍ፤ 2ዲ 1313 2ዲ ሲር 1973) ወይንም ሕግን በማውጣት (ሪስቴትመንት ኦፍ ኮንፍሊክት ኦፍ ሎውስ ቁጥር 98) 1973 እና ዩናይትድ ስቴትስ ቁጥር 481 (1987) 1966፣ ገጽ 34

42 ዶናልድ ፒ· ባልኬ፣ የሕጉች ግጭት፤ የውጭ አገር ፍርዶች ውጤቶች በዓመት አራቴ የሚታተም የኮርኔል የሕግ መጽሔት፣ ቮልዩም 12፤ 1926–271 ገጽ 62–66·

43 የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር የሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 458(ለ)

ሀገሮች የተለያዩ ችግሮቻቸውንና ግጭቶቻቸውን የሚፈቱባቸው የተለያዩ ተቋሞችን ያቋቁማሉ። የባሕር ፍርድ ቤቶች፣ የቤተዘመድ ዳኞች ጉባዔ፣ የቤተ ክህነት ፍርድ ቤቶች፣ የሸሪያ ፍርድ ቤቶች፣ የግል ገላጋዮች፣ ከተቋሞቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። አንድ ውሣኔ ለኢትዮጵያ ሥርዓተ ሕግ እንግዳ በሆነ የውጭ አገር ፍርድ ቤት ቢሰጥ በዚህ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ትክክለኛ አመሠራረትና ሕጋዊነት አለው በማለት የተሰጠውን ፍርድ ሊያስፈጽም ይገባዋልን? የውጭ ሀገር ፍርድ ቤቱ በትክክለኛ ሁኔታ መቋቋሙንና ሕጋዊነቱን ለመመርመር ከተወሰነ ይህ በምን ሕግ መሠረት ሊታይ ይገባል?

በአንድ ሀገር ውስጥ በሕግ መሠረት የተቋቋመ ፍርድ ቤት በሌላው ሀገር ፈፅሞ እንግዳ ሆኖ ሊገኝ ይችላል። ስለዚህም የአንድ ሀገርን ፍርድ ቤት ሕጋዊ አቋም በሌላኛው ሀገር ሕግ ላይ ተመሥርቶ መገምገሙ ምናልባት አሳማኝ ላይሆን ይችላል። በዚህ ፀሐፊ አመለካከት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት የሚችሉት አሳማኝ አቅጣጫ ፍርዱን የሰጠውን ፍርድ ቤት ሀገር ሕግ መሠረት በማድረግ ፍርድ ቤቱ ትክክለኛ አመሠራረትና ሕጋዊነት አለው ወይንስ የለውም የሚለውን መወሰን ነው።

በተመሳሳዩም ሌላው ለመፍታት አስቸጋሪ የሚሆነው ጉዳይ ፍርዱን የሰጠው የውጭ አገር ፍርድ ቤት ሕጋዊ ብቃት እንዳለው ማረጋገጡ ነው። ለምሳሌ ይህንን ሀሳባዊ ምሳሌ እንመልከት። በፈረንሳይ ሀገር በሚገኝ አንድ ፍርድ ቤት የተወሰነለት አንድ ግለሰብ በኢትዮጵያ ፍርዱ እንዲፈፀምለት ያመለክታል። የፈረንሳይ ፍርድ ቤት በፈረንሳይ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 14 መሠረት ተከሳሹ የፈረንሳይ ዜግነት ወይንም ኗሪነት ያለው ቢሆንም ባይሆንም በተከሳሹ ላይ ሥልጣን ስላለው ውሳኔውን ቢሰጥና ይህ ደግሞ በተከሳሹ ኗሪነትና ዜግነት ሁኔታ ላይ ከተመሠረተው የኢትዮጵያ የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን መሠረተ ሀሳብ ጋር ቢጋጭ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የውሳኔውን ተፈፃሚነት ወደ ጎን ሊለው ይችላል ወይስ አይችልም? በጉዳዩ ላይ የፈረንሳይ ፍርድ ቤት ሥልጣን እንዳለው መወሰን ያለበት የየትኛው ሀገር ሕግ ነው? የሚለው ጥያቄ ከዚሁ የሚመነጭ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ የሚናገረው የለም። በዚህ ሁኔታም ላይ በፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች የዳበረ ልምድ የለም።

የፍርድ ቤትን የዳኝነት ሥልጣን ለመወሰን ዛሬ በዓለም ላይ የተለያዩ ብዙ ዘዴዎች እንዳሉ ይታያል።[44] በእንግሎ አሜሪካን የሕግ ሥርዓትና በብዙ የደቡብ አሜሪካ አገሮች ሕግ መሠረት የዳኝነት ሥልጣን የሚወሰነው ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት በሚገኝበት አገር ሕግ መሠረት ነው።[45]

የኮንቲኔንታል የሕግ ሥርዓትን የሚከተሉት እንደ ግሪክ[46]፣ ቱርክ[47]፣ እና ኦስትሪያ[48] የመሳሰሉት ሀገሮች እንደሚጠቀሙበት አሠራር ከሆነ የፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን የሚወሰነው ጉዳዩ እንዲፈጸም በተጠየቀበት ሀገር ሕግ መሠረት ነው። ለምሳሌ በስዊድን አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ዕውቅና ሊኖረውና ተፈፃሚነትን ሊያገኝ የሚችለው ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት እንደ ስዊድን ፍርድ ቤቶች የተቋቋመ ሲሆንና ውሣኔውን የሰጠበት ሕጋዊ ድጋፍ ከስዊድን የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ ጋር ያልተቃረነ ሲሆን ነው[49]።

እንደ ቬንዙዌላ ባሉ ሌሎች ሀገሮች የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን የሚለካው በዓለም አቀፍ መመዘኛ መሠረት ነው[50]። በፈረንሳይ ሕግ ደግሞ አንድ የውጭ ፍርድ ቤት በአንድ ጉዳይ ላይ ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ የሚታየው መንታ አፍ (double barrelled)

---

44 ጂ ጂ ካስል፣ ጁሪስድክሽን ኤንድ መኒ ጀጅመንትስ ሬንደርድ አብሮድ፣ የአሜሪካና የፈረንሳይ ልምድ ንጽጽር፣ ሜጊል የሕግ መጽሔት፣ ቮልዩም 4፣ 1957፣ ገጽ 153–157

45 ኢስታቫን ዛዚ፣ ገጽ 269 የፓል ግሪፍዝ ጋርላንድ መጽሐፍን ገጽ 94 ተመልከት፣ እንዲሁም በ1960 የታተመውን የአልፍሬዶ ኤችቤሪን መጽሐፍ ገጽ 6 ተመልከት

46 አልበርት ኤ· ኤሬንዝዋይግ ቻራላምቦስ ፍራጊታስ እና አትናስዩስ ኪያኖ ጉሎስ፣ የአሜሪካና የግሪክ የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ፣ 1957 ገጽ 31

47 ታርጉ አንሴ፣ የአሜሪካና የቱርክ ዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ 1966፣ ገጽ 69

48 ኢግናዝ ሴድል ሆኤንቬልዳርን የአሜሪካን የኦስትሪያ የግለሰቦች የዓለም አቀፍ ሕግ 1963 ገጽ 96

49 ሀካን ኒያል የአሜሪካና የስዊድን ዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ 1965 ገጽ 69

50 ሪቻርድ ኤስ· ሎምባርድ ገጽ 99–100፣ የዎልተር ኤስ ጆንሰን የሕጎች ግጭት 2ኛ እትም፣ 1962 ገጽ 761ንም ይመልከቱ

በመባል በሚጠራ መሠረተ ሀሳብ ነው። በዚህ መሠረተ ሀሳብ አንድ የውጭ ፍርድ ቤት የሚከተሉትን እንዲያሟላ ይጠበቅበታል። እነዚህም፡ ሀ)ፍርዱን በሚያስፈጽመው ሀገር የተቀመጡ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸውን የዓለም አቀፍ ግለሰቦች ሕግ ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላትና ለ) ፍርዱን በሰጠው ሀገር ሕግ መሠረት ሀገራዊ የዳኝነት ሥልጣን ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ የሚሉት ናቸው[51]።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የአሠራር ደንቦች ሁሉም የራሳቸው ችግሮች ስላሏቸው በራሳቸው እንደተሟሉ የመፍትሔ መንገዶች ለኢትዮጵያ ተስማሚ ናቸው ተብለው የሚጠቆሙ አይሆኑም። የፍርድ ቤት ሥልጣን የሚለካው ፍርዱን በሚሰጠው ሀገር ሕግ ከሆነ የሚከተለው ሁኔታ ሊከሰት ይችላል። አንድ የፈረንሳይ ፍርድ ቤት በፈረንሳይ ግዛት ውስጥ ነዋሪ ባልሆነ ተከሳሽ ላይ ያለውን የዳኝነት ሥልጣን በመጠቀም በግለሰቡ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ፍርድ ሰጠ እንበል። በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት በግለሰብ ላይ ተፈፃሚነት በሚኖራቸው ፍርዶች የፍርድ ቤቱ ሥልጣን የሚወሰነው በተከሳሹ የኗሪነት ክልል መሠረት በመሆኑ ይህንን ቅደመ ሁኔታ የማይጠብቅ በፈረንሳይ ሀገር ፍርድ ቤት የተሰጠን ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ ማስፈጸም የራሱ የሆነ ችግር ያስከትላል። በሌላ በኩል ደግሞ ፍርድ እንዲያስፈጽም በተጠየቀው ፍርድ ቤት ሀገር ሕግ ፍርዱን የሰጠው የውጭ አገር ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ማግኘት ያለበት ሥልጣን ነገር ይታይ ከተባለ አሰራሩ አንድ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መኖር በቂ በራሱ ሀገር ሕግ ብቻ ነው የሚለውንና የሀገራዊ ሕግ መኖር ለዳኝነት ሥልጣኑ መኖር በቂ ማስረጃ ነው የሚሉትን መርሆዎች የሚቃረን ይሆናል።

የፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን መወሰን ያለብን ከዓለም አቀፍ ሕግ አንፃር መሆን አለበት የሚለውም አቋም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ስለሌለው የሚያስኬድ ላይሆን ይችላል። የፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣንን በተመለከተ ዓለም አቀፍ ትርጉሜን ለመፍጠር የተደረገ ሙከራ ቢኖር እ.ኤ.አ. በ1929 የቡስታሜንትን ሕግ (Bustamente Code) ለማርቀቅ የተደረገው ሲሆን ይህም ቢሆን እንኳንስ ዓለም አቀፍ እውቅናን ሊያገኝ ቀርቶ ረቂቁን በአዘጋጁት የላቲን አሜሪካ ሀገሮች እንኳን ሙሉ በሙሉ ድጋፍ ሊያገኝ አልቻለም[52]።

ኢትዮጵያ በጉዳዩ ላይ የምትወስደውን ምርጫ በተመለከተ የግድ ከላይ የጠቀስናቸውንና ሌሎች ሊነሱ የሚችሉ ችግሮችን ያገናዘበ አስታራቂ መንገድ መከተሉ ይበጃል። በተገቢ ሁኔታዎች የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ፍርዱን በሰጠው ሀገር ሕግ መሠረት የሚወሰነውን የብቃት መለኪያ መከተል ይችላሉ።[53] ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ መሬትና በኢትዮጵያ መንግሥት በተሰጠ የፓቴንት መብት ላይ በሚነሱ ጉዳዮች ሀገራዊ ፍርድ ቤቶችን ሥልጣን እንዳያሳጣ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል። የአንድ የውጭ ሀገር ፍርድ ቤት የሥልጣን ክልል የማግኘቱ ጉዳይም ቢሆን ከዓለም አቀፍ ሕግ መርሆዎች ጋር የሚጻረር መሆን የለበትም። በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድ የኢትዮጵያን ፍላጎት የሚጎዳ ከሆነ ወይም በጉዳዩ ላይ ሙሉ ሥልጣን ይኖረዋል ተብሎ የሚታመነው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ከሆነ በውጭ ሀገሩ ፍርድ ቤት የተሰጠው ፍርድ የተፈፃሚነት ጥያቄ ውድቅ ሊሆን ይችላል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ቆየት ያለ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውጭ ሀገር ፍርድን ተፈፃሚነት ውድቅ ያደረገበትን ብይን መመልከቱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።[54] አንድ የሕንድ ዜጋ የሚቆጣጠረው በኢትዮጵያ ክልል ወስጥ የሚገኝ መሬትን በተመለከተ በሕንድ ሀገር የቦንቤ ፍርድ ቤት ፍርድ ሰጥቶበት ብይኑ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ለአፈጻጸም ቀርቦ ነበር። ፍርድ ቤቱም በሰጠው ውሣኔ መሠረት አንድ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መሬትን በተመለከተ የሚደረግ ሽያጭ መከሄድ ያለበት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ከመሆኑም በላይ ጉዳዩም የግድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት መታየት አለበት የሚል አቋም ይዞ ነበር።

---

51 ጆርጅ አር ዴሉም የአሜሪካና የፈረንሳይ ዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ፣ 1960 ገጽ 160

52 የሀቫና የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ኮንቬንሽን፣ 1928፣ ይህ ኮንቬንሽን የቡስታመንቴ ኮድ (Bustamante Code) ተብሎ የሚጠራ ሲሆን በ15 በደቡብ አሜሪካ ሀገሮች ተፈርሟል።

53 አርተር ኑስባውም፣ ጁሪስዲክሽን ኤንድ ፎሬን ጀጅመንትስ፣ በአመት አራቴ የሚታተም ኮሎምቢያ የሕግ መጽሔት፣ ቮልዩም 14፣ 1941፣ ገጽ 221

54 ኖርማን ቤንትዊች፣ ፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው ኢን ኢትዮጵያ፣ በአመት አራቴ የሚታተም የኢንተርናሽናል የሕግ መጽሔት፣ ቮልዩም 4፣ 1951 ገጽ 114

## የፍርድ ባለዕዳ ከፍርድ ቤት ፊት ቀርቦ ራሱን የሚከላከልበት ሁኔታ

በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የፍርዱ ባለዕዳ ከፍርድ ቤት ፊት እንዲቀርብና እራሱን የሚከላከልበት ዕድል የመስጠት ሁኔታ በውጭ አገር የተሰጡ ፍርዶች ተፈፃሚነት ከማግኘታቸው በፊት ሊሟሉ ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ነው[55]። ስለዚህም ሕጉ እንደሚለው ከሆነ በተገቢው ጊዜ ግለሰቡ መጥሪያ ሊሰጠው ይገባል። የፍርዱ ባለዕዳ በጊዜው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በተገቢው ሁኔታ ማስታወቅ ሲቻል ይህ ሳይሆን በመቅረቱ ምክንያት ግለሰቡ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ቢቀር በውጭ ሀገር የተሰጠው ፍርድ ተፈፃሚነቱን ሊያጣ ይችላል[56]።

በዓለም አቀፍ ሕግና ልምድ መሠረት አንድ ተከሳሽ በቂ በሆነ ጊዜ የፍርዱ መሠረት የሆኑትን ዶኩሜንቶች እንዲያውቃቸው ካልተደረገ ፍርዱ ተፈፃሚነትን ከቶ ሊያገኝ አይችልም። ፍርዱን የሰጠው የውጭ ሀገር ፍርድ ቤት ተከሳሽ የክሱን ጭብጥ አውቆት እራሱን እንዲከላከልበት በቂ ጊዜ ሊሰጠው ይገባል። በተጨማሪም የሚያዛቸው ነገሮች ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ፍርድ ቤቱ መጀመሪያውኑ ሥልጣን ሊኖረው ይገባል። በግለሰብ ላይ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችል የዳኝነት ሥልጣን ሳይኖር የሚሰጥ ማንኛውም ዓይነት ፍርድ በዓለም አቀፍ ሕግ ከቶውኑም ተቀባይነት የለውም[57]።

በኮመን ሎው (Common law) ሕግ በራሱ ፈቃድ አንድ ግለሰብ ፍርድ ቤት ካልቀረበና በስምምነት ወይንም በአንድ ኩባንያ ውስጥ የአክሲዮን ባለቤት በመሆኑ ለፍርድ ቤቱ ሥልጣን ተገዢ ካልሆነ በስተቀር[58] በሌሎቹ ሁናቴዎች ሁሉ ግለሰቡ በሚኖርበት ቦታ የጥሪ ወይንም የማስታወቂያ መንገዶችን ማመቻቸት እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ ተቀምጧል። የእንግሊዝ አገር ፍርድ ቤቶች መንግሥት በዜጎቹ ወይንም በክልሉ ውስጥ በሚኖሩ የውጭ ዜጐች ግለሰቦች ላይ ካልሆነ በስተቀር ከክልሉ ውጭ በሆኑ ግለሰቦች ላይ ሥልጣን ሊኖረው አይችልም የሚል አቋም አላቸው። የሆነ ሆኖ አንድ የፍርድ ባለዕዳ እራሱን የመከላከል ዕድል ተሰጥቶት ዕድሉን ሳይጠቀምበት ቀርቶ ፍርድ ቤቱ ግለሰቡ በሌለበት ፍርድ ቢሰጥ ፍርዱ የዳኝነት ሥልጣን በሌለበት ሁኔታ የተሰጠ ነው ተብሎ ወደ ጎን ሊገፋ አይችልም።

በዓለም አቀፍ ሕግ ለተከሣሾች መጥሪያ ሊሰጥ የሚገባው የውጭ ሀገሩን ፍርድ በሰጠው ፍርድ ቤት ሀገር ሕግ መሠረት ነው። አንድ በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድ ዕውቅና እንዲያገኝ ወይም እንዲፈጸም ጥያቄ ሲቀርብ ፍርድ ሰጪው የውጭ ፍርድ ቤት ለተከሣሾች መጥሪያዎችን ለመስጠት የተከተለው ሥርዓት ፍርዱን በሚያስጽመውም ፍርድ ቤትም ዘንድ ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል። የመጥሪያ አሰጣጡ ባሕርይ መሠረታዊ ትክክለኘነት የለውም የሚያሰኝ መሆን አይኖርበትም። ተከራካሪው ተገቢ የሆነ መጥሪያ አልተሰጠውም ተብሎ በውጭ ሀገር የተሰጠውን ፍርድ እንዲያስፈጽም በቀረበለት ፍርድ ቤት የታመነ ከሆነ ይኸው ፍርድ ተፈፃሚነትን እንዲያገኝ አይደረግም።[59]

## በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ መጨረሻነትና ተፈፃሚነቱ

በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት በአራተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችለው ቅድመ ሁኔታ የውጭ ውሣኔው መጨረሻና ተፈፃሚነት ሊያገኝ የሚችል መሆን አለበት የሚለው ነው[60]። ይህንን ቅድመ ሁኔታ በምናይበት ገዜ ሊነሱ የሚችሉ አንድ አንድ ጥያቄዎች ይኖራሉ። መጨረሻና ተፈፃሚነት ሊያገኝ የሚችል ውሣኔ ማለት ምን ማለት ነው? መጨረሻና ተፈፃሚነት ያላቸው በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት የተሰጡ ፍርዶች የሚባሉትስ እንዴት ዓይነት ያሉት ፍርዶች ናቸው? የፍርዱን መጨረሻነትና ተፈፃሚነት ለመወሰን የምንጠቀመው

55 የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር የሥነ ሥርዓት ሕግ፣ አንቀጽ 458(ሐ)
56 ሮበርት ኤ. ሲድለር ገጽ 110–119
57 ምርቶን የሕጎች ግጭት 3ኛ እትም፣ ገጽ 649
58 አር ኤች ግራቭሰን፣ 1969፣ ገጽ 665–667
59 ስታቫን ዛዚ ገጽ 574
60 የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር የሥነሥርዓት ሕግ አንቀጽ 458(መ)

የየትኛውን ሀገር ሕግ መሠረት በማድረግ ነው? የሚሉት ሊነሱ ከሚችሉት ጥያቄዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

ከላይ በሌሎችም ጉዳዮች ላይ እንዳየነው ሁሉ የኢትዮጵያ ሕግ ይህንን በተመለከተ እምብዛም የሚናገረው ነገር የለም። ምንም ዓይነት የፍርድ ቤት ልምድ በጉዳዩ ላይ ያለመኖሩ ደግሞ ችግሩን በይበልጥ አባብሶታል። ስለዚህም የውጭ ሀገሮችን ሕጎችና የፍርድ ቤቶች ልምድ ማገናዘብ ከፍተኛ ዕርዳታ ይሰጣል።

መጨረሻነትና ለተፈፃሚነት ብቁ መሆን የሚያስገነዝበን ነገር ቢኖር አንድ ፍርድ በማንኛውም ፍርድ ቤት እንደገና ሊታይና ሊለወጥ ወይንም ደግሞ ወይኅን ሊባል አለመቻሉን ነው[61]። እንደ እንግሊዛዊው ዳኛ ሎርድ ሄርቾል ከሆነ መጨረሻነት የሚፈጠረው አንድ ፍርድ በቂ በሆነ መልኩ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የመብቶችን ሕልውና ሲያረጋግጥ ነው[62]።

በአንድ መጨረሻና ለመፈፀም በቂ ሆኖ በተሰጠ ፍርድ ተከራካሪ ወገኖች ሁሉ ሊገዙበት ይገባል[63]። ስለ አንድ ውሣኔ መጨረሻነት በምናወራበት ጊዜ ይግባኝ የተጠየቀበት ፍርድ፣ አንደኛው ተከራካሪ ባልተገኘበት ሁኔታ የተሰጠ ፍርድ (በኢትዮጵያ ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት ፍርድ ትዕዛዝና ውሣኔን ያካትታል)[64]፣ አፈጻጸም ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት የታገደ ፍርድ፣ የካሣ ክፍያ መጠኑ ወይም ዓይነቱ ያልተወሰነበት ፍርድ፣ በፊት የተሰጠ ትዕዛዝ፣ ለመተዳደሪያ የሚሆን ገንዘብ እንዲከፈል የሚሰጥ ውሣኔና የሕፃናትን ማሳደግ በሚመለከት የሚሰጥ ፍርድን ሁሉ ሊያካትት ይችላል።

አንድ የውጭ ፍርድ ተፈፃሚነት የሚኖረው የመጨረሻ ፍርድ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለሆነ በይግባኝ ወይንም እንደገና በመመርመር ላይ ያለ ፍርድ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሁሉ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ውድቅ ይሆናሉ። ፍርዱን የሰጠው የውጭ ፍርድ ቤት ብቃት ካለው፣ የፍርዱ ባለዕዳ እራሱን የሚከላከልበትን ዕድል ፍርድ ቤቱ እስከሰጠው ወይም በተገቢው ጊዜ ውስጥ ፍርዱን በመቃወም ፍርዱን ለሰጠው የውጭ ሀገር ፍርድ ተቃውሞ እስከአቀረበ ድረስ የፍርዱ ባለዕዳ ፍርድ ቤት ባለመቅረቡ ግለሰቡ በሌለበት የሚሰጥ ማንኛውም ፍርድ የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያለው ነው ተብሎ ይወሰዳል[65]።

የመጨረሻና ይግባኝ ሊባልበት የማይችል ፍርድ ተሰጥቶ ነገር ግን ፍርዱ የታገደ እንደሆነ፣ ምንም እንኳን በአንዳንድ ፍርድ ቤቶች ይህ በሚጣራበት ወቅት ከሳሹ ፍርዱ እንዲፈፀምለት የመጠየቅ መብት የለውም የሚለውን አቋም ቢያዙም በአጠቃላይ ያለው የአሠራር ልምድ የሚያረጋግጠው ግን ከሳሹ ይህን የመሰለ ጥያቄ ለማንሳት እንደሚችል ነው። ነገር ግን ጉዳዩ ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት እልባት እስካገኘ ጊዜ ድረስ ፍርዱ እውቅናና ተፈፃሚነት እንዲያገኝ የተጠየቀበት ሀገር ለተወሰነ ጊዜ ከተፈፃሚነት ሊያግደው ይችላል[66]። ይህን የመሰለው እገዳ ፍርዱ በተከታይነት በሚሰጥ ፍርድ ቁርጠኛ ሆኖ እስከሚታወቅ ድረስ የሚቀጥል ይሆናል[67]።

ከፍርድ በፊት የሚሰጡ ውሣኔዎች፣ ለመተዳደሪያ የሚሆን ገንዘብ እንዲከፈል የሚሰጥ ፍርድና የሕፃናትን ማሳደግ በሚመለከት የሚሰጥ ፍርድ መጨረሻነትና ተፈፃሚነት ችግሮች ግልጽ ሆነው ከሚታዩባቸው ጉዳዮች አንዳንዶቹ ናቸው። ከፍርድ በፊት የሚሰጥ ውሣኔን በተመለከተ የተለመደው አሠራር ውሣኔው ከመጨረሻው ፍርድ ጋር አብሮ ወይም ቀደም ብሎ የተሰጠ የመሆኑ ጉዳይ ነው[68]። በእርግጥ ከመጨረሻው ፍርድ ቀደም ብሎ የተሰጠ ማንኛውም ትዕዛዝ በራሱ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም። ነገር ግን የመጨረሻው ፍርድ

---

61 ዎልተር ኤስ ጆንሰን፣ የሕጎች ግጭት፣ 2ኛ እትም 1962 ገጽ 758 759

62 ኑቪዮን እና ፍሪማን፣ 15 የይግባኝ ጉዳይ 1፣ የሎው ኳርተርሊ ሪቪው፣ ቮሊዩም 6፣ 1890፣ ገጽ 238 ይመልከቱ

63 ጂ.ኤች ሲ. ሞሪስ ኮንፍሊክት ኦፍ ሎው፣ ዘጠነኛ እትም 1973፣ ገጽ 1039

64 የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነሥርዓት ሕግ፣ አንቀጽ 3

65 ጃ.ሲ. ቼሻየር ዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ፣ 2ኛ እትም 1961 ገጽ 659.

66 ኖትስ አንድ ሌጂስሌሽን፣ ዘፋይናሊቲ ኦፍ ጀጅሜንትስ ኢንዘኮንፍሊክት ኦፍ ሎውስ፣ የኮሎምቢያ የሕግ መጽሔት ቮልዩም 41፣ 1941፣ ገጽ 889.

67 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 889 890

68 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 887 889

አካል ሆኖ የተሰጠ ትዕዛዝ ከሆነ ይኸው ትዕዛዝ የመጨረሻና ተፈፃሚ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል[69]።

ሕፃናትን ማሳደግ በሚመለከት የሚሰጥ ፍርድን የተመለከትን እንደሆነ ያለው አጠቃላይ የአሠራር ልምድ እንደሚያሳየው ፍርዱ የሚለወጥ ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ ተፈፃሚነትን ያገኛል[70]። ለመተዳደሪያ የሚሆን ገንዘብ እንዲከፈል የሚሰጥ ፍርድ፣ በተያያዘ መልኩ ጊዜያቸው የተላለፈባቸው ወይም ተከታታይ ክፍያዎችን በሚመለከት የተሰጡ ፍርዶች የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያላቸው ስለመሆኑ በአንዳንድ ፍርድ ቤቶች ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቷል[71]። የመጨረሻነትና የተፈፃሚነት ጥያቄዎች ሕፃናት ማሳደግን በተመለከተ ጉዳይ ላይም ሊነሱ ይችላሉ። በዚህ ረገድ የተለመደው አሠራር የሚጠቀመው ውሣኔው የልጁን ከሁሉ የተሻለ ጥቅም ያገናዘበ መሆን እንዳለበት ነው[72]።

የፍርዶች መጨረሻነትና ተፈጻሚነት በየትኛው አገር ሕግ መሠረት ይወሰን የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ ዓለም አቀፍ እውቅና ያላቸው ሁለት አሠራሮች አሉ[73]። በአንደኛው አሠራር መሠረት የፍርዶች ተፈፃሚነት መለካት ያለበት ፍርዱን በሰጠው ሀገር ሕግ መሆን ሲኖርበት በሁለተኛው ሥርዓተ ልምድ ግን ጉዳዩ መወሰን ያለበት ፍርዱ ተፈፃሚነትን እንዲያገኝ በተጠየቀበት ሀገር ሕግ መሠረት ነው። ምንም እንኳን ግልጽ የሆኑ ድንጋጌዎች በኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ ተቀምጠው ባይገኙም በውጭ ሀገር የተሰጠው ፍርድ በዚሁ ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይንም ሬጂስትራር መረጋገጥ አለበት የሚለው ቅድመ ሁኔታ ኢትዮጵያ እየተከተለች ያለችው መስመር የመጀመሪያው መሆኑን ያሳያል[74]።

## የሕዝብ ሞራልና ፀጥታ

እንደሌሎች ሀገሮች ሁሉ[75] በኢትዮጵያም ሕግ የሕዝብ ሞራልና ፀጥታ ጉዳይ ለአንድ በውጭ ሀገር ለሚሰጥ ፍርድ መፈጸም እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ ተቀምጧል[76]። የሕዝብ ፀጥታ በተለያዩ ምክንያቶች ተፈፃሚነት እንዲያገኙ የማይፈለጉ ፍርዶችን ለማገድ እንደ አንድ የመቆጣጠሪያ መሣሪያ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል[77]። የሕዝቦችን ባሕል፣ ልማድና አመለካከት በሚጥስ ሁኔታ ፍርዶች ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸው የሞራል ቅድመ ሁኔታ እንደዚሁ እንደ አንድ የመከላከያ ዘዴ ሆኖ ያገለግላል። የአንድ ሀገር የሞራል ሕግና ደንብን የሚቃረን አሠራር ሁሉ ፀጥታን የሚያናጋ በመሆኑ በአጠቃላይ በሕዝብ ፀጥታ ቅድመ ሁኔታ ላይ ማተኮሩ ጠቀሜታው ከፍ ያለ በመሆኑ[78] የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በዚሁ የሕዝብ ፀጥታ መሠረተ ሀሳብ ላይ ያተኩራል።

---

69 አርተር ቮንመኸረን እና ዶናልድ ቲ ትሮትማን፣ የውጭ ብይኖችን እውቅና የመስጠት ሁኔታ ጥናትና የመፍትሔ መንገዶችን ጠቋሚ ሀርቫርድ የሕግ መጽሔት ቮልዩም 81፣ 1968 ገጽ 58·

70 ጂ ኤች ሲ ሞሪስ፣ ገጽ 103

71 ጂ ጂ ቼሻየር ገጽ 661

72 ኖትስ ኤንድ ሌጂስሌሽን፣ ዘፋይናሊቲ ኦፍ ጀጅመንትስ ኢን ዘኮንፍሊክት ኦፍ ሎውስ የኮሎምቢያ የሕግ መጽሔት ቮልዩም 41፣ 1941፣ ገጽ 887 888

73 ዝኒ ከማሁ ገጽ 566

74 የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 457(ለ)

75 ስቴቨን ዛዚ፣ ኮንፍሊክት ሎውስ ኢን ኢሮፕያን ዲሞክራሲስ፣1964 ገጽ 160 170

76 የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ፣ አንቀጽ 458(ሠ)

77 ሲቲቨን ዛዚ፣ ገጽ 279፣ ዊሊያም ኢ ሆልደር፣ ፐብሊክ ፖሊሲ ኤንድ ናሽናል ፕሬፈረንስስ፣ ዘ ኤክስክሉዥን ኦፍ ፎሬን ሎው ኢንግሊሽ ፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው፣ ኢንተርናሽናል ኤንድ ኮምፓረቲቭ ሕግ መጽሔት፣ 1968፣ ቮልዩም 17 ክፍል 4፣ ገጽ 926 929

78 ስቴቨን ዛዚ ገጽ 578 | እንዲሁም በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 71 የተጻፈውን ምንጭ ይመል ከቱ|

የሕዝብ ፀጥታ ለሚለው ቃል ትርጓሜ ለመስጠት አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ከዚህ በፊት የተደረጉ ብዙ ሙከራዎች ሁሉ ሳይሳካላቸው ቀርተዋል ለማለት ይቻላል[79]። ነገር ግን ቃሉና ፅንሰ ሐሳቡ እጅግ የዳበረ በመሆኑ በተለያዩ ሀገሮች ባሕል፡ ሞራል፡ ሶሻልና ኢኮኖሚ ሥርዓቶች እንዲሁም በየሀገሮች ሕገ መንግሥቶችና ሕጎች እንዲሁም በፍርድ ቤቶች አሠራር በይበልጥ ሲገለፅ ይታያል[80]። የአንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ተፈፃሚነት እነዚህን በመሰሉ በተለያዩ መሠረታዊ ሐሳቦች፣ ሕጐችና የፍርድ ቤቶች አሠራር የሚገለጠውን የሕዝብ ፀጥታ የሚቃረን ከሆነ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። ይህ አቋም በኢትዮጵያ ያለጥርጥር ተቀባይነት አለው።

የሕዝብ ወይም የመንግሥት ፖሊሲ በመባል የሚታወቀው የሕዝብ ፀጥታ መርህ በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶች ተፈፃሚነት እንዳያገኙ በማድረግ በኩል ከፍተኛ የሆነ ሚና ይጫወታል። ዳይሲ እና ሞሪስ እንደሚሉት፡

> "በውጭ ሀገር ሕግ መሠረት የተገኘ መብት፡ ሥልጣን፡ ችሎታ፡ ጉድለት ወይም ሕጋዊ ግንኙነት በእንግሊዝ ሕግ ውስጥ ተቀባይነት ከአለው መሠረታዊ ፖሊሲ ጋር የሚቃረን ከሆነ የእንግሊዝ ፍርድ ቤት መብቱን፡ ሥልጣኑን፡ ችሎታውን፡ ጉድለቱን ወይም ሕጋዊ ግንኙነቱን አያስፈጽምም ወይም ዕውቅና አይሰጠውም[81]።"

የእያንዳንዱ ሀገር ሕግ እንደሚያሳየው የሕዝብ ፀጥታን መርህ እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ በራሱ በውጭ ሀገር የተሰጠን ፍርድ ተፈጻሚነትን ለማገድ ያረዳል። ፍርዱን እንዲያስፈጽም ጥያቄ በቀረበለት ፍርድ ቤት ዘንድ ተቀባይነት የሌለውና የውጭ ፍርድ የተመሠረተበት ሕግ ተፈጻሚነት እንዳያገኝ ለማድረግ ያስችላል። የውጭ አገር ፍርድ ለመሠጠቱ መሠረት በሆነው የውጭ አገር ሕግ ተፈጻሚነት የተነሣ ኢፍትሐዊነትንና ሌሎች መሰል ከባድ ችግሮችን የሚያስከትሉ ሁኔታዎችን ለመከላከል ያስችላል።

በኢትዮጵያ በሕግም ሆነ በፍርድ ቤቶች ውሣኔ ውስጥ የሕዝብ ፀጥታን ጥያቄ ሊያስነሱ የሚችሉ ሁኔታዎች በዝርዝር የተቀመጡበት የለም። ነገር ግን እንደፀሐፊው እምነት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉአቸው ዓለም አቀፋዊ እውቅናን ያገኙ አንዳንድ የሕዝብ ፀጥታን ጥያቄ በማንሳት ፍርድን ከተፈፃሚነት የሚያግዱ ምክንያቶች አሉ።

አንደኛ አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ፣ ፍርዱን በሰጠው በዚሁ ፍርድ ቤት ወይንም የፍርዱ ተጠቃሚ በሆነው ግለሰብ ያላግባብ በሆነ የማጭበርበር ድርጊት የተገኘ ከሆነ ይህ ፍርድ ተፈፃሚነት አያገኝም።[82] ለምሣሌ ፍርዱ የተሰጠው በሀሰት ማስረጃ ላይ ተመርኩዞ ከሆነ፡ ቢታወቁ ኖሮ የፍርዱን ውጤት ሊቀይሩ የሚችሉ እውነታዎች ሳይገለፁ በመቅረታቸው[83] ወይም ደግሞ ፍርዱን የሰጡት ዳኞች በውሣኔው ውጤት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ጥቅም እንዳላቸው ከተረጋገጠ ፍርዱ ያለአግባብ ተገኝቷል ወይንም ደግሞ የሕዝብ ፀጥታን ተቃርኗል ተብሎ ውድቅ ሊሆን ይችላል[84]።

በእንግሊዝ የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ በማጭበርበር የተሰጠ ወይም የተገኘ መሆን የለበትም የሚለው እራሱን እንደቻለ አንድ ቅድመ ሁኔታ ተቀምጧል[85]። የፍርዱ ባለዕዳም ቢሆን ፍርዱ በተጭበረበረ መንገድ ተገኝቷል በማለት ፍርዱ ተፈፃሚነት እንዳያገኝ ይግባኝ ሊል ይችላል። ስለዚህም የፍርዱ ተፈፃሚነት

---

79 ከላይ በተገለጸው ማስታወሻ 2 ገጽ 279 ኔልሰን ኤኖን ቾንግ የሕዝብ ፖሊሲ በሕጎች ግጭት ውስጥ፡ የቻይና ግንብ በትንሺ እንገሊዝ ዘሪያ ኢንተርናሽናልና የኮምፓራቲቭ ሎው ኳርተር ቮልዩም 45፡ ክፍል 3፡ 1966፡ ገጽ 634 637

80 የሕዝብ ፖሊሲ መሠረተ ሀሳብ በሕጎች ግጭት፣ የኮሎምቢያ የሕግ መጽሔት፣ ቮልዩም 33፣1933 ገጽ 514

81 ዳይሲ እና ሞሪስ፡ የሕጎች ግጭት፡ 8ኛ እትም፣ 1967፡ ገጽ 72

82 ዘ አሜሪካን ስቴትመንት ኦፍ ኮንፍሊክት ኦፍ ሎው፣ 1934፣ በአንቀጽ 440 (ሀ) የተሰጠ አስተያየት

83 ስቴሽን ዛዚ፡ ገጽ 278

84 ኤች ግሪቭንሰን፡ ኮንፍሊክት ኦፍ ሎውስ 6ኛ እትም፡ 1969 ገጽ 674 675

85 ማሩሲያ ባርንሬድ፡ የውጭ ውሣኔዎች ተቀባይነትና አፈፃፀም፡ ኢንተርናሽናል ኤንድ ኮምፓራቲቭ ሎው ኳርተርሊ፡ ቮልዩም 3፡ ክፍል 1፣ 1954 ገጽ 49 50

የተጠየቀበት ፍርድ ቤት ውሣኔውን በሰጠው ፍርድ ቤት የታዩትን ማስረጃዎችና የተሰጡትን ፍርዶች እንደገና መርምሮ ውሣኔ ሊሰጥባቸው ይችላል[86]። ለምሣሌ ፍርዱ የተፈረደለት ግለሰብ አሳሳች ማስረጃ አቅርቧል ወይንም ደግሞ ፍርዱን የሰጡት ዳኞች በጉዳዩ ላይ ግላዊ ጥቅም አላቸው ብለው እስካመኑበት ድረስ የእንግሊዝ ፍርድ ቤቶች ፍርዱን ከተፈፃሚነት ውድቅ ያደርጉታል። የኢትዮጵያን አቋም የተመለከትን እንደሆነ ከላይ የተጠቀሱት ቅድመ ሁኔታዎች በሕዝብ ፀጥታ መሠረተ ሀሳብ ውስጥ የተካተቱ ስለሆነ አሰራሩ ከላይ ያለውን መልክ የያዘ ነው ለማለት ይቻላል።

*ሁለተኛ* በሚፈጽመው የሰብዓዊ መብትና ነፃነት ረገጣ ሳቢያ የዓለም ማሕበረሰብ ያገለለውና ከዚህ የተነሳ ኢትዮጵያ በዕኑ የምትቃወመው ሀገር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ ተፈፃሚ እንዳይሆን ሊደረግ ይቻላል[87]። በተጨማሪም ከቤተኛ አዳሪነት የሚገኝ ጠቀሜታን፣ ከቁማር የመነጨ ዕዳን፣ ከዕፅ ሽያጭ የሚገኙ ጥቅማ ጥቅሞችንና እንዲሁም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሕገ ወጥ ከሆኑ ማንኛውም እንቅስቃሴዎች የሚገኙ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ የተሰጡ ፍርዶች በኢትዮጵያ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም[88]።

*ሦስተኛ* በኢትዮጵያ ውስጥ በዚያው ጉዳይ ላይ በኋላም ቢሆን የሚሰጥ ተቃራኒ ውሣኔን የሚቃወም የውጭ ውሣኔ ተቀባይነት አይኖረውም[89]። በፍትሐብሔሩ የሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ የተሰጠን ፍርድ የሚቃረን በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ፣ ምንም እንኳ የውጭ ሀገሩ ፍርድ ቀድሞ የተሰጠ ቢሆንም ተቀባይነት አይኖረውም።[90]

*አራተኛ* የመንግሥት ሕግ ባሕርይ ያላቸው የአስተዳደር[91]፣ የታክስ[92] እና እንዲሁም የወንጀል[93] የውጭ ሀገር ፍርዶች ከቶውኑም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ሊፈፅሙ አይችሉም። በአጠቃላይ ከዓለም አቀፍ ሕግ መሠረተ ሀሳቦች አንፃር በውጭ ሀገር የሚሰጡ ፍርዶች ተፈፃሚነት ሊኖራቸው የሚችለው በፍትሐ ብሔርና በንግድ ላይ ያተኩሩ ጉዳዮች ሲሆኑ ብቻ ነው። የመንግሥት ሕግ ባሕርይ ያላቸው በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶች ሁሉ ፍርዱን የሰጠው ሀገር መንግሥታዊ ፍላጎት የሚያንፀባርቁ በመሆናቸው እንደ ነፃና ሉዓላዊ የሆነ ሌላ ሀገር ውሳኔውን ለማስፈፀም ወኪል አይሆንም።

የድንበር ተሻጋሪነት መሠረተ ሀሳብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባገኘበትና በብዙ ፍርድ ሰጭ አካሎች ድጋፍ ባገኘበት በአሁኑ ወቅት ፍርድ ቤቶች በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት የተሰጠን የወንጀል ፍርድ ያስፈፅማሉ ማለት ምንአልባት ከዕውነት የራቀ ነው ለማለት ይቻላል።[94] የእንግሊዝን ፍርድ ቤቶች በተመለከተ ቼሻየር እንደሚለው ከሆነ የእንግሊዝ ፍርድ ቤቶች ከክልል ውጭ የተሰጠውን የወንጀል ፍርድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለማስፈፀም የሚያስችል ክፍተት መስጠት የለባቸውም[95]።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ከወንጀል ፍርዶች ጋር ተያይዘው የሚወሰኑ የፍትሐ ብሔር ውሣኔዎችን የሚመለከት ይሆናል። ለምሳሌ እንደ በውጭ ሀገር የሚገኝ የወንጀል ፍርድ ቤት ለወንጀሉ ቀጥተኛ ሰለባ የሚወሰነውን ካሣ በተመለከተ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ውሣኔውን ይቀበሉታልን? የሚለው አንዱ ጥያቄ ነው። ከብዙ ሀገሮች ልምድ እንደምንረዳው ብዙ ፍርድ ቤቶች ይህንን መሰል የፍትሐ ብሔር ገጽታ

---

86 ዜልማን ኮዌን፣ የውጭ ውሣኔዎችና ማታለልን የሚመለከት መከላከያ፣ ሎው ኳርተርሊ ሪቪው፣ ቮልዩም 65፣ 1949፣ ገጽ 82 86

87 ኢያን ብራውንሊ፣ የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረተ ሀሳቦች፣ ሁለተኛው እትም፣ 1973 ገጽ 101 08

88 የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ 1952፣ ቁጥር 1716

89 ስቴቫን ዛዚ፣ ገጽ 279፣ የቬንዙዌላ የፍትሐ ብሔር የሥነ ሥርዓት ሕግ 1916፣ አንቀጽ 748(4) ይመልከቱ

90 የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነሥርዓት ሕግ፣ አንቀጽ 8(2)

91 የአሜሪካን የሕጎች ግጭት ስቴትመንት ክፍል 443

92 አልበርት ኤ ኤረንዝዊንግ እና ኤሪክ ጃይም ገጽ 79 80

93 ዝኒ ከማሁ

94 የሎተስ ጉዳይ (1927) ፒ.ሲ. አይ. ጄ ቁጥር 10.

95 የቼሻየር የዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግ፣ 7ኛ እትም፣ 1965 ገጽ 329

ያለውን ፍርድ የሚያስፈጽሙ በመሆኑ[96] የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችም በጉዳዩ ላይ ለየት ያለ አቋም ሊይዙበት የሚችሉበት ሁኔታ የለም። በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የካሣ ጥያቄ ለብቻው በፍትሐ ብሔር ችሎት ወይም ከወንጀሉ ጋር ተጣምሮ በወንጀል ችሎት መታየት የሚችልበት ሁኔታ አለ[97]። በመሆኑም የካሣ ውሣኔው በፍትሐ ብሔር ችሎት ወይም በወንጀል ችሎት መታየቱ አንዳች ለውጥ ሊያስከትል አይገባም። ውሣኔው በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ተፈፃሚነትን ሊያገኝ ይገባል።

በውጭ ሀገር የተሰጠ የግብር ፍርድን በተመለከተ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የገቢ ሕግ መርሀ ፍርዶቹ ዕውቅና እንዳይሰጣቸውና ተቀባይነትም እንዳይኖራቸው ይደነግጋል። ለምሳሌ በዩናይትድ ስቴትስ የገቢ ሕግን የሚያጣቅሱ ፍርዶች ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸው ይደረጋሉ[98]። በኢትዮጵያም የግብር ሕግን መሠረት ያደረጉ በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶች የሕዝብ ፀጥታን ይፃረራሉ ተብሎ ስለሚታመንባቸው ከተፈፃሚነት ውድቅ ይሆናሉ።

## ማጠቃለያ

እንደማንኛውም የዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ አባል ሀገር ሁሉ፣ እያደገ በመምጣት ላይ የሚገኘው ዓለም አቀፍ ግንኙነትና ትስስር ኢትዮጵያ በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶችን እንደማስፈፀም የመሰሉ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መፍትሔ እንድታዘጋጅ ያስገድዳታል። ኢትዮጵያ በፍርድ ቤቶቿ የሚሰጡ ፍርዶች በሌሎች ሀገሮች ፍርድ ቤቶች ተፈፃሚነት እንዲያገኙ እንደምትፈልግ ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ በውጭ ሀገር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ፍርዶች በኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈፀሙ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይኖርባታል። በፍርድ ቤቶች አካባቢ የሚታየውን በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶችን ከመፈፀም ጋር ተያይዘው ያሉትን ችግሮች ለማቅለል ኢትዮጵያ ከምንም ጊዜ በላይ በአሁኑ ወቅት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች እንደገና መከለስና ማየት ይኖርባታል።

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በተለይ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 458 ውስጥ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች አፈጻጸም በተመለከተ አስፈላጊው መሻሻል ይደረግባቸው ዘንድ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ይላል። ቅድመ ሁኔታዎቹ ያለ አንዳች ችግር በፍርድ ቤቶች ዘንድ በሥራ እንዲተረጎሙ መከለስ ይገባቸዋል። አሁን ባሉበት ሁኔታ ቅድመ ሁኔታዎቹ የሌሎች አገሮች ሕጎች ማድረግ እንደሚያስችሉት የሕግ ጥያቄዎችን ለመፍታት በቂ አይደሉም። በውጭ ሀገር የተሰጡ ፍርዶችን አፈጻጸም የሚመለከቱትን የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች በማሻሻል ኢትዮጵያ ሊያጋጥሟት የሚችሉትን የዓለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ ችግሮች ለመቋቋም ከወዲሁ ዝግጁ ሆና መገኘት ይኖርባታል።

---

96 ኢግናዝ ሴዲል ሆሄንቬልደርን፣ ገጽ 113

97 የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ 19 አንቀጽ 100

98 በንግሥቲቱና በጊልበርት መካከል በተነሳው ክርክር፣ 497 ኤፍ ቱዲ 1161 (9ኛ ሰር፣ 1979 አንድ የአራተኛ ፍርድ ቤት በአራተኛ ዜጎች ላይ የተሰጠን የእንግሊዝ ኩሉምቢያ የታክስ ውሣኔ የሬቨኑ ሕግን (Revenue Rule) መሠረት በማድረግ ተፈፃሚ እንዳይሆን አግዷል።